ዘመን ባንክ
Zemen BANK

# ለዘመን ባንክ አ.ማ ባለአክሲዮኖች በሙሉ
# የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማና የምርጫ ሂደት መስፈርቶችን
# ለማሳወቅ የወጣ ማስታወቂያ

ዘመን ባንክ አ.ማ. ማክሰኞ መስከረም 26 ቀን 2019 ዓ.ም በአዲስ ኢንተርናሽናል ኮንቬንሽን ሴንተር ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ጀምሮ በሚያካሂደው 18ኛ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ባንኩን ለቀጣይ ሦስት ዓመታት የሚያስተዳደሩ 12 አባላት የሚኖሩት የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የኩባንያ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 መሰረት ያካሂዳል። ስለሆነም ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት እጩ ሆነው መቅረብና መመረጥ የሚችሉት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት የሚገባቸው መሆኑን ባንኩ በአክብሮት ያስታውቃል።

## 1. በሁሉም ባለአክሲዮኖች ለሚጠቆሙና ለሚመረጡ ዕጩ የቦርድ ዳይሬክተሮች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

1. ቢያንስ ለሁለት ዓመት የባንኩ ባለአክሲዮን የነበረ/ች፤
2. የባንኩ ቦርድ አባል ሆኖ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነ/ች እና ሐላፊነቱ/ቷን በአግባቡ ለመወጣት በቂ ጊዜ ያለው/ያላት፤
3. የሌላ ማንኛውም ባንክ ሠራተኛ ያልሆነ/ች፤
4. ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው/ያላት ወይም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋም ተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ እውቅና ያገኘ/ች፤
5. በባንኪንግ፣ በፋይናንስ፣ በሪስክ ማኔጅመንት፣ በአካውንቲንግ፣ በማኔጅመንት፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሕግ፣ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን፣ በኦዲቲንግ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና በተዛማጅ የሙያ ዘርፍ ቢያንስ 7 (ሰባት) ዓመት የሥራ ልምድ ያለው/ያላት፤
6. የሌላ የፋይናንስ ተቋም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ያልሆነ/ች፤
7. በሌሎች ከአራት በበለጡ ተቋማት ውስጥ የቦርድ አባል በመሆን በማገልገል ላይ የማይገኝ/ትገኝ፤
8. በኢትዮጵያም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ በእምነት ማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀል ተከሶ/ተከሳ በፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ያልተሰጠበት/ያልተሰጠባት፤
9. እራሱ/ሷ ወይም እሱ/ሷ በዋና ባለቤትነት የያዘው/ችው ድርጅት ወይም ተፅዕኖ ማሳደር የሚችልበት/የምትችልበት ድርጅት በፍርድ ቤት ወይም አስተዳዳራዊ የዳኝነት ስልጣን ባለው አካል ወይም በመንግስት ተቆጣጣሪ አካላት እምነት በመጣስ ጉዳዩች ላይ ተመርምሮ፣ ታግዶ ወይም ተቀጥቶ የማያውቅ፤
10. እራሱ/ሷ ወይም እሱ/ሷ በዋና ባለቤትነት የያዘው/ችው ድርጅት ወይም ተፅዕኖ ማሳደር የሚችልበት/የምትችልበት ድርጅት ወይም በዳይሬክተርነት ወይም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ባለቤት የሆነበት/ችበት ድርጅት የባንክ ወይም የሌላ ብድር ግዴታውን ወይም የታክስ ክፍያውን ባለመክፈል ተከሶ/ሳ ጥፋተኛ ያልተባለ/ች ወይም ንብረቱ/ቷ በሃራጅ ያልተሸጠበት/ባት፤
11. እራሱ/ሷ ወይም እሱ/ሷ በዋና ባለቤትነት የያዘው/ችው ድርጅት ወይም ተፅዕኖ ማሳደር የሚችልበት/የምትችልበት ድርጅት ወይም በዳይሬክተርነት ወይም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ባለቤት የሆነበት/ችበት ድርጅት ስልጣን ባለው ተቆጣጣሪ የመንግስት አካል የተጠየቀውን/ችውን መረጃ ያልደበቀ/ች፤ የተሳሳተ የፋይናንስ ወይም ሌሎች መግለጫዎች ያላቀረበ/ች ወይም የተቆጣጣሪ አካላት ውሳኔ ላለመቀበል ወይም ላለመገዛት እምቢተኛ ሆኖ የማያውቅ/የማታውቅ፤
12. እራሱ/ሷ ወይም እሱ/ሷ በዋና ባለቤትነት የያዘው/ችው ድርጅት ወይም ተፅዕኖ ማሳደር የሚችልበት/የምትችልበት ድርጅት ወይም በዳይሬክተርነት ወይም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ባለቤት የሆነበት/ችበት ድርጅት በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ከማንኛውም የፋይናንስ ተቋም የተበላሸ የብድር ታሪክ የሌለው፤
13. ባለአክሲዮኑ/ኗ አክሲዮን የገዛበትን/ችበትን ገንዘብ ያገኘው/ችው ከከሰረ ሰው ወይም በአስተዳደር ችግር ምክንያት ኪሳራ ካጋጠመው ሰው ያልሆነ ወይም ገንዘቡን ያገኘው/ችው በማጭበርበር ወይም በህገወጥ መንገድ ያልሆነ፤
14. አግባብነት ባለው የብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት በቂ ስንቅ ሳይኖረው/ራት ቼክ በመፃፍ የባንክ ሂሳቡ/ቧ ያልተዘጋበት/ባት፤
15. ባለአክሲዮኑ/ኗ የአክሲዮን ባለቤት በሆነ/ች ጊዜ የነበረው/ራት የሀብት መጠን ከአክሲዮኖቹ ዋጋ በላይ የነበረ፤
16. ሃቀኛ፣ ታማኝ እና መልካም ስም ያለው/ላት፤ በተለይም በማጭበርበር፣ እምነት በማጉደል፣ ትክክለኛ ያልሆነ የሂሳብ መግለጫ በማቅረብና በመሳሰሉት ተከሶ/ሳ በፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶበት/ባት የማያውቅ/ታውቅ፤
17. ከዚህ በፊት በንግድ ማኅበር አደራጅነት፣ ዳይሬክተርነት፣ ሥራ አስኪያጅነት፣ ተቆጣጣሪነት፣ ኦዲተርነት ወይም በሌሎች የአመራር ሐላፊነቶች ላይ ተመድቦ/ባ ሲሰራ/ስትሰራ ከሐላፊነታቸው ጋር በተያያዘ ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ በእምነት ማጉደል፣ በስርቆት ወይም ለቦርድ አባልነት ብቁ በማያደርግ ተመሳሳይ ወንጀል ጥፋተኛ ያልተባለ/ች፤
18. በራሱ/ሷ ወይም በሚመራው/በምትመራው ወይም ዳይሬክተር በሆነበት/ችበት ድርጅት ላይ የመክሰር ክስ ያልቀረበበት/ባት ወይም የኪሳራ ውሳኔ ያልተሰጠበት/ባት፣ በኪሳራ ምክንያት ንብረቱ/ቷ ለዕዳ ማቻቻያነት ያልዋለበት/ባት፤
19. የባንክ ብድር ባለመክፈሉ/ሏ ምክንያት ንብረቱ/ቷ በሐራጅ ያልተሸጠ፣ ተከሶ/ሳ ያልተፈረደበት/ያልተፈረደባት ወይም እሱ/ሷ የሚመራው/የምትመራው ወይም ዳይሬክተር የሆነበት/ችበት ድርጅት ከገንዘብ ተቋማት የተበደረውን/ችውን ገንዘብ ባለመክፈሉ ብድሩ ወደ ጤናማ ያልሆነ የብድር ደረጃ ያልዞረበት/ያልገባበት/ባት፤
20. በንግድ ሕግ፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወጡ መመሪያዎች እና በሌሎች ህጎች ላይ የተገለፁ ሌሎች መስፈርቶች መሟላት አለባቸው።

## 2. ገለልተኛ ዕጩ የቦርድ ዳይሬክተሮችን በተመለከተ

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እና በህግ የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ገለልተኛ ዕጩ ዳይሬክተሮች በዳይሬክተሮች ቦርድ ተመልምለው በአስመራጭ ኮሚቴው አማካይነት ለምርጫ ይቀርባሉ።

### ማሳሰቢያ

- የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር አስራ ሁለት /12/ ሲሆን፤ በገለልተኛ የቦርድ አባልነት አራት /4/ እንዲሁም ገለልተኛ ባልሆኑ የቦርድ አባልነት ስምንት /8/ ዳይሬክተሮች በዕለቱ ይመረጣሉ፤
- ከገለልተኛ ቦርድ አባላት (Independent Directors) ዕጩዎች በስተቀር የሌሎች የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ የሚካሄደው በመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤው ዕለት ነው፤
- ዘመን ባንክ አ.ማ ተጽዕኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮኖች የሌሉት በመሆኑ ሁሉም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በዕለቱ በተገኙት ባለአክሲዮኖች ይመረጣሉ፤
- በዕለቱ አምስት አባላት ያሉት የዳይሬክተሮች ቦርድ ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ በጉባዔው ይመረጣል፤
- የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት በቦርድ አባልነት መመረጥ አይችሉም። የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የባንኩ ሠራተኞች የአስመራጭ ኮሚቴው አባል ሆነው መመረጥ አይችሉም፤
- አንድ ባለአክሲዮን ራሱን በእጩነት በመጠቆም በምርጫው ላይ መወዳደር ይችላል።
- ሦስት ዓመት ያገለገሉ ነባር የቦርድ አባላት በድጋሚ መመረጥ ይችላሉ፤
- ከአጠቃላይ የቦርድ አባላት ውስጥ ቢያንስ ሁለት ሴቶች በቦርድ አባልነት መመረጥ አለባቸው፤
- ከማህበሩ ጸሐፊ ውጭ ሁለት የባንኩ ሠራተኞች የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆነው ሊመረጡ ይችላሉ።
- የባንኩ ቦርድ አባላት እና የባንኩ ሠራተኞች ባለአክሲዮኖችን ወክለው ድምፅ መስጠት አይችሉም።
- የሚጠቆመው እና የሚመረጠው የቦርድ አባል ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ ድርጅቱን በመወከል በቦርድ አባልነት የሚያገለግለው/የምታገለግለው ሰው ማንነት መታወቅ እና ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ/የምታሟላ መሆን ይኖርበታል/ባታል።

**ዘመን ባንክ አክሲዮን ማኅበር**

Call Center 6500
www.zemenbank.com
info@zemenbank.com

**የላቀ አገልግሎት ማዕከል**